27

723/2013

852 መ28/38
5/13/2005

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ከ/ል/ኮ/ሚ

ጉዳዩ፣ የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፣

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የኢግዚቢሽን ዝግጅት መመሪያ ቁጥር 27/2005 ሆኖ ከጳጉሜ 1 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታቃል።

በዚሁ መሠረት መመሪያውን እንድታስፈጽሙ የፀደቀው መመሪያ 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጐ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሠንዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድትከታተሉት እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ፣

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ከተማ ልማት ዘርፍ/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ኮንስትራክሽን ዘርፍ/
- ለህብት ሥራ አመራርና ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለህግ አገልግሎት መምሪያ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት አብይ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት ቴክኒክ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት ኤግዚቢሽን ንኡስ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት የከተሞች ምዝገባ፣ ጥሪና መስተንግዶ ንኡስ ኮሚቴ

ከ/ል/ኮ/ሚ

05/13/05

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት

ETHIOPIAN CITIES WEEK

## 5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት የኤግዚቢሽን ዝግጅት መመሪያ ቁጥር 27/ 2005

ጳጉሜ / 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን እና የከተማ ልማት ፕሮግራሞችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ አመታዊ የከተሞች ሣምንት የተሰየመ ሲሆን የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት በተለያዩ ከተሞች አስተናጋጅነት በየአመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይከበራል፡፡

ከኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት አበይት ክንውኖች መሀከል ከተሞችን የማስተዋወቅ ስራ አንዱ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ከተሞችም ባለፉት ዓመታት በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ከፍተኛ ዕድገት ያስመዘገቡበትና ለሃገራዊ ምጣኔ ሃብት የሚሰጡት ግብዓት ከፍ ያለበት ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን ይህም ከተሞች ለኢንቨስትመንት፣ ለገበያ፣ ለቱሪዝም ወዘተ በራቸውን ክፍት ማድረግና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ያገኙት ውጤት ነው፡፡ በቀጣይነትም ከተሞቻችን እርስ በእርስ ብቻ ሳይሆን ከዓለም ከተሞችም ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ውድድር ከተሞች ዕድገታቸውን ለማፋጠንና የነዋሪዎቻቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ ብቃት ያለው ራስን የማስተዋወቅ (professional city marketing) ስራን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህም ከተሞች ከመቼውም ይበልጥ በተደራጀና ዓለም ዓቀፍ የጥራት ደረጃን በጠበቀ መልኩ ራሳቸውን የማስተዋወቅ እና የመሸጥ ስራን አጠናክረው ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ይህንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የከተሞቻችንን ራስን የማስተዋወቅ ስራ ለማገዝ ይቻል ዘንድ ሃገር አቀፍ የኢትዮጵያ ከተሞች ኤግዚቢሽንን በፕሮግራሞቹ አካቷል፡፡

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ኤግዚቢሽንን በሚመለከት ለተሳታፊ ከተሞች ጠቃሚ መረጃ በመስጠት እንዲሁም የአዘጋጆችን፣ የተባባሪዎችን እንዲሁም የተሳታፊዎችን ሚና በመለየት በባህር ዳር ከተማ ለአምስተኛ ጊዜ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ኤግዚቢሽን የሚመራበትን ስርአት ለመደንገግ የተዘጋጀ ነው፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የ5ኛው የከተሞች ሳምንት የኢግዚቢሽን ዝግጅት መመሪያ ቁጥር 27 /2005 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአምስተኛው የከተሞች ሳምንት አዘጋጆች፣ ተባባሪ አዘጋጆችና ተሳታፊ ከተሞች እንዲሁም በዝግጅቱ ለሚሳተፉ ሌሎች የመንግስትና የግል ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

### 3. የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ኤግዚቢሽን ዓላማዎች

1) ከተሞች የልማት ስራዎቻቸውን የሚያሳዩበት፣ እርስ በእርስ የሚማማሩበት፣ ለኗሪዎቻቸው እና ለሌሎች ባለ ድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃ የሚሰጡበት እንዲሁም የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም፣ የገበያ እና ሌሎች መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት መድረክ በመፍጠር ለዕድገታቸው መፋጠን አጋዥ የሚሆኑ ግብአቶችን እንዲያገኙ ማስቻል ነው፣
2) ከተሞች ራሳቸውን በብቃት በማስተዋወቅ የእርስ በርስ ጤናማ የውድድር መንፈስ ለማዳበር ነው።

### 4. ከኤግዚቢሽኑ የሚጠበቁ ውጤቶች

1) ስለከተሞች የልማት ሂደት እና ስለደረሱበት የዕድገት ደረጃ በነዋሪዎች እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ዘንድ ትክክለኛ ግንዛቤ ይፈጠራል፣
2) ከተሞች የልማት መስህቦቻቸውን በማስተዋወቅ ከኢንቨስትመንት፣ ቱሪዝም፣ ገበያ .... ወዘተ ተጠቃሚነታቸው ይጨምራል፣
3) ከተማን የማስተዋወቅ ሂደት እና ጥቅሞቹን በሚመለከት ግንዛቤ ይፈጠራል፣ ብሎም ከተሞች የማስተዋወቅ ስራን እንደ አንድ ዓብይ ተግባር እንዲወስዱት ምቹ ሁኔታን ይፈጠራል፣
4) የመረጃ ልውውጥን በማጠናከር በከተሞች እና በኗሪዎቻቸው መሀከል ያለው መግባባት እና ትስስር ይጠናከራል በዚህም ለስራ የከተማ ህዝብ ንቅናቄ አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል።

### 5. የኤግዚቢሽኑ ወቅት እና ቦታ

5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ኤግዚቢሽን ከህዳር 11-17/ 2006 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ ይካሄዳል።

# ክፍል - ሁለት

## የተሳታፊ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 6. የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች

1) ከተሞች

የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ኤግዚቢሽን ከያዘው ሰፊ ከተማን የማስተዋወቅ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ ግንዛቤን የማስጨበጥ ዓላማ አኳያ ለሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ክፍት ነው:: በ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ኤግዚቢሽን ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ ከ140 በላይ ከተሞች እንደሚሳተፉ ይጠበቃል::

2) ሌሎች ተሳታፊ ባለድርሻ አካላት

ከከተሞች በተጨማሪ ለከተማ ልማት ዘርፉ አጋዥ የሆኑ ባለድርሻ አካላት በኤግዚቢሽኑ መሳተፍ ይችላሉ:: እነዚህም፦

ሀ/ የክልል ከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ቢሮዎች፣

ለ/ አግባብነት ያላቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣

ሐ/ አግባብነት ያላቸው የክልል ቢሮዎች፣

መ/ የጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት፣

ሠ/ የቴክኒክና ሙያ እና የከፍትኛ ትምህርት ተቋማት፣

ረ/ የግል እና የመንግስት የኮንስትራክሽን ተቋማት፣

ሰ/ የፋይናንስ ተቋማት፣

ሸ/ አግባብነት ያላቸው የግልና የመንግስት ዘርፍ መ/ቤቶች፣

ቀ/ በከተማ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት፣

በ/ አለም አቀፍ እህት ከተሞች፤

ተ/አለም አቀፍ ድርጅቶች፣

ቸ/ በኤች አይ ቪ ኤድስ፣በስነ ተዋልዶና ማህራዊ ጉዳይ የተሰማሩ ድርጅቶች ናቸው::

## 7. ዋና አዘጋጆች

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ኤግዚቢሽን ዋና አዘጋጆች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ እና የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ናቸው::: በዚህ ዝግጅት GIZ የበኩሉን አስተዋጽኦ ጋደርጋል::

## 8. ተባባሪ አዘጋጆች

1) የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ኤግዚቢሽን ጥራቱን በጠበቀና የከተሞች ሣምንትን አላማ በሚያሰካ መልኩ ማከናወን ይቻል ዘንድ በኤግዚቢሽን ዝግጅት በቂ ችሎታና ልምድ ያላቸውን ድርጅቶች በጨረታ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡
2) የኤግዚቢሽን አስተባባሪው የሚመረጠው ግልጽ በሆነ የውድድር መስፈርት እና ሂደት ብቻ ነው፡
3) በጨረታ የተመረጠው ድርጅት የሚጠበቅበትን ተግባር በበቂ ሁኔታ መፈጸም ይኖርበታል፡ በሚወጣው መርሀ ግብር መሰረት ከሚኒስቴር መስሪያቤቱ ጋር ይፈራረማል፤

## 9. የ5ኛው የከተሞች ሳምንት ኤግዚቢሽን ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፤

1) የኤግዚቢሽኑን መሪ ዕቅድ ያዘጋጃል፡ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
2) ስለኤግዚቢሽኑ ኦፊሺያል መግለጫ ከመዝናኛ ዝግጅቶችና የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ጋር በመሆን አዘጋጅቶ መግለጫ ይሰጣል፤
3) የኤግዚቢሽኑን ተባባሪ አዘጋጅ የስራ ዝርዝር ቢጋር ያዘጋጃል፤
4) የኢግዚቢሽን ተባባሪ አዘጋጅ ቅጥር እንዲከናወን ያደርጋል፤
5) ለተሳታፊዎች ስለኤግዚቢሽኑ መረጃ ይሰጣል፤
6) ለኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች የሚከራይ አነስተኛ የቦታ መጠን ይወስናል፤
7) ኤግዚቢሽኑ የሚያርፍበትን ቦታ አርክቴክቸራል ፕላን **በግዢ ህግ መሰረት** በባለሙያ ያሰራል፡ ያጸድቃል፤
8) የኤግዚቢሽን ተሳታፊዎችንና የሚፈለጉትን የቦታ መጠን **ከ5ኛው የከተሞች ጥሪ፣ ከመስተንግዶና ከእንግዶች ጥሪ** ንዑስ ኮሚቴ በመረከብ ጥያቄያቸውን መሰረት **በማድረግ** የቦታ ድልድል ይወስናል፤
9) የኤግዚቢሽን አስተባባሪው በሥራ ዝርዝሩ ሠረት ተግባሩን ማከናወኑን ይከታተላል፤ የኤግዚቢሽኑን አፈጻጸምም ይቆጣጠራል፤

## 10. የ5ኛው የከተሞች ሳምንት አስተናጋጇ የባህርዳር ከተማ ተግባርና ኃላፊነት

1) ለኤግዚብሽን ዝግጅት **ከ**10 **ሄክታር** ያላነሰ በቂና አመቺ ቦታ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤
2) ለኤግዚቢሽን ቦታ አስፈላጊ የሆኑ እንደ በቂ የኤሌክትሪክ ሀይል ቆጣሪ (3 phase)፡ ውሀ ቆጣሪ ፡ የመኪና ማቆምያ፡ የመጸዳጃ ቤቶች፤ አጥር ወዘተ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ያቀርባል፤
3) የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ፡ አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ መከላከያ ያቀርባል፤
4) የተጠናከረ የጥበቃ ሥራ በማከናወን የኤግዘቢሽኑን ተሳታፊዎች እና የንብረቶቻቸውን ደህንነት ያስከብራል፤
5) ኤግዚቢሽኑን በከተማው ህዝብ በስፋት እንዲጎበኝ **ለከተማው ነዋሪ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አደረጃጀቶች፣ ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም** የዩንቨርሲቲ ማህበረሰብ የቅስቀሳ ስራ ያከናውናል፤

## 11. የየ5ኛው የከተሞች ሳምንት ኤግዚቢሽኑ ተባባሪ አዘጋጅ ተግባርና ኃላፊነት

1) ለኤግዚቢሽኑ ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ እንደ ድንኳን፣ ፓርቲሽን፣ የድንኳን ውስጥ የኤሌክተሪክ መስመር ዝርጋታ፣ ጠረጴዛና ወንበር ወዘተ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችንና ሌሎች የኤግዚቢሽን ኢጋዥ መሳሪያዎችን ያቀርባል፣
2) የተሳታፊዎችን ጥያቄ ባገናዘበ መልኩ የቦታ ድልድል ያካሂዳል ይህንኑም ለንኡስ ኮሚቴው አቅርቦ ያፀድቃል፣
3) በቦታ ድልድሉ እና በአርኪቴክቸራል ፕላኑ መሰረት የድንኳን እና የፓርቲሽን ተከላ እና የቦታ ድልድል ያከናውናል፣
4) የድንኳን እና ፓርቲሽን ተከላ፣ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ የመሳሰሉ አቅርቦቶችን ቢያንስ ከኤግዚቢሽኑ መከፈቻ 2 ቀናት በፊት ያጠናቅቃል፣
5) ኤግዚቢሽኑ የሚካሄድበትን ቦታ የማስዋብ ስራ ይሰራል፣
6) ተሳታፊዎች ኤግዚቢሽናቸውን በሚገነቡበት ወቅት አስፈላጊው የኤግዚቢሽን ግንባታ ያቀርባል፣ ለግንባታውም ድጋፍ ይሰጣል፣
7) ለከተሞች ኤግዚቢሽን ዝግጅት ሞያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
8) ለተሳታፊ ከተሞች አስጎብኚዎች ስለእንግዶች አቀባበልና ገለጻ አሰጣጥ አጭር ስልጠና ይሰጣል፣
9) ተሳታፊዎች ከኤግዚቢሽን መከፈቻ ቀን በፊት ዝግጅታቸውን ማጠናቀቃቸውን ያረጋግጣል፣
10) ከኤግዚቢሽኑ በፊት እና በኤግዚቢሽኑ ወቅት ከተሳታፊዎች የሚነሱ ጥያቄዎችን ያስተናግዳል፣
11) ከተሞችና ሌሎች አካላት በኤግዚቢሽኑ እንዲሳተፉ ቅስቀሳ ከሚያደርገው ኮሚቴ ጋር ተናቦ የማስተዋወቅ ስራውን ይደግፋል፣
12) ከበዓሉ መጠናቀቅ ባኋላ ለኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ንብረቶቻቸውን እንዲያነሱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣
13) የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ኤግዚቢሽን በድምቀት እንዲከበር አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል።

## 12. የተሳታፊዎች ከተሞች፣ መ/ቤቶች፣ ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1) የኤግዚቢሽኑን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ እና የኤግዚቢሽን መመሪያው በሚያዘው መሰረት ይዘው የሚቀርቡትን ዝግጅቶች ያደራጃሉ ያጠናቅቃሉ፤
2) በኤግዚቢሽኑ ቦታ ቢያንስ ከሁለት ቀን በፊት ቀድመው በመገኘት ቦታቸውን ይረከባሉ፣ ኤግዚቢሽናቸውንም ይገነባሉ፤አነስተኛ መሳሪያዎችን እንደ ፕላስተር፣ ሁክ ፕላስቲኮች፣ ገመድ፣ ሚስምር፣ ሜትር ወዘተ በራሳቸው ይሸፍናሉ።
3) በበዓሉ ወቅት በኤግዚቢሽኑ ቦታ በመገኘት ለጎብኝዎች መግለጫ ይሰጣሉ፤ ጥያቄዎችን ያስተናግዳሉ፤
4) ከበዓሉ ማጠቃለያ በኋላ የገነቡትን ኤግዚቢሽን እና ንብረቶቻቸውን ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ያነሳሉ፤
5) ኤግዚቢሽናቸውን ለመገንባት እና ለማፍረስ አስፈላጊውን የሰው ኃይል ያቀርባሉ።

## 13. የሁሉም ክልል የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ቢሮዎች /ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1) ሁሉም የክልሉ ከተሞች በበቂ ዝግጅት እንዲሳተፉ ያስተባብራሉ፣ ያነሳሳሉ ለዝግጅቶቻቸውም ድጋፍ ያደርጋሉ፣
2) በከተሞች ሣምንት ዝግጅት ላይ ለመሳተፍ የአቅም ውስንነት ላለባቸው የክልሉ ከተሞች ድጋፍ ያፈላልጋሉ ያስተባብራሉ፣
3) ከክልሉ መገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር የከተሞች ሣምንት ሁነቶች እና የከተሞች ኤግዚቢሽንን በሚመለከት መረጃ ይሰጣሉ ሁነቶቹን በሰፊት ያስተዋውቃሉ።

## ክፍል - ሶስት
## የኤግዚቢሽኑ ይዘት እና ጥራት

## 14. የኤግዚቢሽኑ ይዘት

1) የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት በዋነኝነት በከተሞች፣ በነዋሪዎች እና በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ እና የልምድ ልውውጥ የሚካሄድበት ሲሆን ይዘቱም ከንግድ ወይም ከሸቀጥ ልውውጥ ኤግዚቢሽን የተለየ ነው፤
2) በ13.1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞችም ሆኑ ሌሎች ተሳታፊዎች በኤግዚቢሽኑ ላይ ምርቶቻቸውን ለገበያ ማቅረብ ይችላሉ፤
3) በ13.2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች የሚያቀርቡት ኤግዚቢሽን በዋንኝነት ማንጸባርቅ ያለበት በ13.1 እና 14 የተገለጸውን ይሆናል፤

723/2013

15. የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንትን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ የተሳታፊ ከተሞች ኤግዚቢሽን የሚከተለው ይዘት እና ቅደም ተከተል ይኖረዋል፡፡

| ተ.ቁ | ይዘት | የአቀራረብ ስልት |
|---|---|---|
| 1) | አጠቃላይ የከተማ መረጃ<br>- ስም<br>- የህዝብ ብዛት<br>- ራዕይ…ወዘተ | • በራሪ ወረቀቶች፣ ፎቶግራፎች፣ አጭር ከ3 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ወዘተ<br>• ገፀበረከቶች /የከተማው ልዩ መገለጫ ሃብት/ |
| 2) | ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት | • የተፈጠሩ የስራ እድሎች ጠቋሚ መረጃ /ግራፎች፣ ፖስተሮች ፎቶዎች ወዘተ…<br>• ለናሙና የሚቀርቡ የጥቃቅንና አነስተኛ የምርቶች ውጤት<br>• የወንዶችና የሴቶች እንዲሁም የወጣቶች ተጠቃሚነት |
| 3) | ከተሞች መልካም አስተዳርና አቅም ግንባታ ስራዎች<br>• የነዋሪዎች ተሳትፎና ንቅናቄ፣ በከተሞች አገልግሎት አሰጣጥና የሰው ሀይል ልማት ላይ ያለው ተሞክሮ | • በከተማ ልማት ዘርፎች እና በከተማ አቀፍ እንቅስቃሴዎች የኗሪዎችን ተሳትፎ ኗሪዎች የከተማውን ሰላም ለመጠበቅ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚገልፁ ፎቶግራፎችና ሌሎች ሰነዶች<br>• ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች… በከተማ ልማት ያላቸው ተሳትፎ የሚያሳይ ሰነድ፣<br>• በነዋሪዎች ብቻ፣ ከግልና እና ከመንግስት ተቋማት ጋር የተሰሩ ስራዎች<br>• የከተማው አደረጃጀትና የሚሰጠው አገልግሎት እስከ ቀበሌ ስለመውረዱና ሰው ሀይል ስለመሟላቱ፣<br>• በከተማው አገልግሎት አሰጣጥ ህብረተሰቡ እስተያየት |
| 4) | በመሬት ልማትና ማኔጅንት | • የከተማውን ግንባታና ክፍት ቦታ ለመለየት የተደረገ ጥረት፣<br>• የለማ መሬት፣<br>• ስልማት የቀረበ መሬት<br>• ያስገኘው ገቢ፣ |
| 5) | የመኖሪያ ቤቶች ልማት | • የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሞዴሎች ፎቶግራፎች ከነዋሪዎች ጋር<br>• በግል ሪል ስቴት የተሰሩ ቤቶች<br>• የአቅርቦት እና ፍላጎት ማመሳከሪያ ግልፅ ቻርቶች፣ ፖስተሮች ወዘተ<br>• የቤቶች ልማትን ተከትሎ የተፈጠሩ የስራ ዘርፎች መረጃ እና የስራ ዘርፎች ናሙና ወዘተ<br>• የወንዶችና የሴቶች እንዲሁም የወጣቶች ተጠቃሚነት |
| 6) | የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ | • የግንባታ ህጉን ለመተግበር የተደረገ ጥረት፣<br>• ከተፈቀደው ፕላን ውጪ የተገነቡ ግንባታዎችን ለመከላከል የተደረገ ጥረት፣<br>• የተቋራጮች ህጋዊነት ስለማረጋገጥ |
| 7) | የመሰረተ ልማት ግንባታ/ ማስፋፊያ | • የፕሮጀክቶች ሞዴል ፎቶግራፎች ፖስተሮች ቻርቶች ወዘተ |

723/2013

| ተ.ቁ | ይዘት | የአቀራብ ስልት |
|---|---|---|
| | ስራዎች | ▪ የመሰረተ ልማት መስፋፋትን ተከተሎ የተፈጠሩ የስራ መስኮችና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ፎቶዎች ናሙናዎች ወዘተ<br>▪ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዓይነት እና የነዋሪው ተጠቃሚነት<br>▪ የከተማው የአተገባበር ስልት/ሂደት |
| 8) | የከተማ ፕላን ጽዳትና ውበት | ▪ መዋቅራዊ ፕላኖች<br>▪ የአካባቢዎች ፕላን ሞዴሎች<br>▪ የመሬት ዝግጅትና አቅርቦት ዋና ዋና ክንውኖች የሚገልፁ ግራፎች፣ ፎቶዎች ወዘተ…<br>▪ ከዳስተር የከተማ ካርታዎች ወዘተ…<br>▪ የከተመዋን ጽዳትና ውበት የሚያሳይ ሰነድ፣የመንገድ ላይ፣የአደባባይ፣መናፈሻ ቦታዎች፣ ተቋማት<br>▪ |
| 9) | ኢንቨስትመንት (ታላላቅ) | ▪ የከተማዋ የኢንቨስትመንት መስህቦች<br>▪ በከተማዋ ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎች<br>▪ አሁን ያለው የኢንቨስትመንት መጠን እና ዓይነት መግለጫ<br>▪ የማመልከቻ ቅፃችና ጠቃሚ አድራሻዎች<br>▪ የኢንቨስትመንት ውጤቶች (ለማስተዋወቅ ወይም ለሽያጭ የሚቀርቡ)<br>▪ ባለሀብቶች በከተማው ያላቸውን ኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ |
| 10) | ቱሪዝም/ባህል | ▪ የቱሪስት መስህቦች ፎቶ፣ ማስታወቂያዎች፣ ፊልሞች<br>▪ የቱሪስት መረጃዎች /በራሪ ወረቀቶች ወይም ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጁ ወረቀቶች/<br>▪ የሆቴሎች ዝርዝርና አድራሻ<br>▪ ባህላዊ አለባበሶች<br>▪ ባህላዊ ምግቦች ወይም መጠጦች<br>▪ የከተማውን ባህልና ታሪክ የሚገልጹ ቁሳቁሶች<br>▪ ለተሳታፊዎች የሚሰጡ ስጦታዎች |
| 11) | የከተሞች ፋይናንስ | ▪ የሚጠበቅና የተሰበሰበ የገቢ መጠን ጠቋሚ መረጃዎች<br>▪ በተሻሻለ የፋይናንስ ስርዓት የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳዩ መግለጫዎች /ፎቶግራፍ ፖስተር ፊልም ወዘተ/<br>▪ የፋይናንስ ማኑዋሎችን የግብር ከፋዮች መረጃ ወዘተ. |
| 12) | ሌሎች | ▪ በከተማዋ ወይም በልማት አጋሮች የሽያጭ ወይም ለስጦታ የሚቀርቡ ምርቶች<br>▪ ሌሎች የከተማዋን ሁኔታና ዕድገት የሚጠቁሙ መረጃዎች |

13) የይዘት መመሪያ በዋናኝነት የሚመለከተው ከተሞችን ሲሆን ሌሎች ተሳታፊዎች የሚያቀርቡት ዝግጅት በመሰረቱ ከዚህ የተለየ ባይሆንም ከአንድ ከተማ በላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ለብቻ በተዘጋጀ የኤግዚብሽን ቦታ ሊያቀርቡ ይችላሉ::

## 14 የጥራት መመሪያዎች

14) ተሳታፊ ከተሞች የኤግዚቢሽን አቀራረባቸው ከላይ የተቀመጠውን የይዘት ቅደም ተከተል የጠበቀ መሆን አለበት፣

15) በጽሑፍ የሚቀርቡ መረጃዎች በግልጽ የሚነበቡ እና ግደፈት የሌለባቸው መሆን አለባቸው፣ በተጨማሪም በእጅ ያልተጻፉ እና ባለቀለም ቢሆኑ ይመረጣል፣

16) የመረጃ ቻርቶች ባለቀለም፣ በግልጽ የሚታዩ፣ በእጅ ያልተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፣ በሚታይ ሁኔታ መሰቀል አለባቸው፣ የቻርቶቹ መጠን ከጽ3 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፣

17) የመረጃ ፊልሞች ርዝመት ከ3ደቂቃ በላይ መሆን የለበትም፤

18) ፎቶግራፎች በጥራት የተነሱ ገላጭ እና ለእይታ አመቺ መጠን ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፤

19) ለኤግዚቢሽን የሚቀርቡ የፎቶግራፎች መጠን ከጽ4 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤

20) ተሳታፊ ከተሞች ከኤግዚቢሽናቸው ይዘት በተጨማሪ ጥራት ላለው አቀራረብ በርትተው መስራት ይጠበቅባቸዋል::

## 16. ለጎብኚዎች የሚደረግ ገለጻ

1) ተሳታፊ ከተሞች ከኤግዚቢሽኑ መከፈቻ እስከ መዝጊያው ድረስ ለእንግዶች ተገቢውን ገለጻ የሚያደርጉ ባለሞያዎችን መመደብ ይጠበቅባቸዋል፣

2) ገለጻ ሰጪዎች በኤግዚቢሽኑ አስተባባሪ የሚዘጋጀውን አጭር ሞያዊ ስልጠና መውሰድ አለባቸው፤

3) በመከፈቻው ቀን ለሚገበኙ የከብር እንግዶች የሚሰጥ ገለጻ ከ3 ደቂቃ መብለጥ የለበትም::

## ክፍል - አራት

## የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና የተሳትፎ ክፍያ

### 17. የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ እና አጠቃቀም

1) አንድ ተሳታፊ የሚሰጠው አነስተኛ የቦታ መጠን 12 ካሬ ሜትር ሲሆን ከፍተኛው በከተሞች ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል፤

2) የኤግዚቢሽን ቦታ ድልድል የሚካሄደው ተሳታፊዎች ለከተሞች ጥሪ ፣መስተንግዶ እና እንግዶች ጥሪ ንዑስ ኮሚቴ በሚያቀርቡት የቦታ ጥያቄ መሰረት የኤግዚቢሽን ኮሚቴ መረጃውን ወስዶ ድልድሉን በማከናወን ነው፡፡ ይህም በሚከተለው ሂደት ይከናወናል፡፡

ሀ/ ተሳታፊዎች የሚፈልጉትን ቦታ መጠን ለከተሞች ጥሪ ፣መስተንግዶ እና እንግዶች ጥሪ ንዑስ ኮሚቴ እስከ መስከረም 20/ 2005 ድረስ ያሳውቃሉ፣

ለ/ የሚፈልገው ቦታ መጠን ተቀባይነት ያለው ከሆነ ተሳታፊው የሚጠበቅበትን ክፍያ እስከ ጥቅምት 10 ቀን 2006 ድረስ ገቢ ማድረግ ይጠበቅበታል፤

ሐ/ ተሳታፊዎች የሚጠይቁት የቦታ መጠን ከሚፈቀደው ከፍተኛ የቦታ መጠን በላይ ከሆነ እንደ አስፈላጊነቱ በንኡስ ኮሚቴው ውሳኔ ተሰጥቶበት አስፈላጊውን ክፍያ እንዲፈፅሙ ይደረጋል፤

መ/ ማንኛውም ተሳታፊ በኤግዚቢሽኑ ቦታ የተዘጋጀለትን ቦታ ለመረከብ የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ ወይም የባንክ የገንዘብ ትራንስፈር ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

ሠ/ ለተሳታፊዎች የሚሰጠው ቦታ በእጣ ትልልቅና ትናንሽ ከተሞችን በማቀላቀል ይደለደላል፤

### 18. የተሳትፎ ክፍያ

1) በኤግዚቢሽኑ ለመሳተፍ፡

ሀ/ የምዝገባ ክፍያ ብር 1000፣

ለ/ የቦታ ኪራይ ለአንድ ቀን በካሬ ሜትር ብር 150 መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡

2) ተሳታፊዎች የሚከራዩት ቦታ ከ12 ካሬ ሜትር ያነሰ መሆን የለበትም፤

3) ተሳታፊዎች የኤግዚቢሽን ቦታውን የሚከራዩት ለ7 ቀን ነው፤

4) ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አካላት የቦታ ክፍያ አይመለከታቸውም፡-

ሀ/ የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን አዘጋጆችና ተባባሪ አዘጋጆች፤

ለ/ የከተሞች የምርጥ ተሞክሮ ውድድር ዲስፕሌይ፤

ሐ/ የኤች አይ ቪ ግንዛቤ ማስጨበጫና የበጎ ፈቃደኝነት ምርመራ፤

መ/ የመዝናኛ ዝግጅቶች አቅራቢዎች፤

ሠ/ ያለክፍያ ተመጣጣኝ የድንኳን መጠን የሚሰጣቸው ድርጅቶች፣መስሪያቤቶችና ተቋማት ካለው ቦታ አንጻር ታይቶ በ5ኛው የከተሞች ሳምንት ቴክኒክ ኮሚቴ ሲወሰን ይችላል፡፡ሠ/ የባርዳር ከተማ አስተዳደር አዘጋጅ ከተማ በመሆኖ 500 ካሬ ሜትር በነጻ የሚሰጣት ሲሆን የቦታ ምርጫዋም ይጠበቅላታል፡፡

5) የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ከኤግዚቢሽኑ መከፈቻ 2 ቀን በፊት ቦታቸውን ይረከባሉ፡

6) የኢግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ኢግዚቢሽኑ ከሚከፈትበት ቀን ዋዜማ የዲስፕሌይ ዝግጅቶቻቸውን ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡ በኤግዚቢሽኑ መከፈቻ ወቅት ማንኛውንም የግንባታ እና የዲስፕሌይ ዝግጅት ማከናወን በጥብቅ የተከለከለ ነው፤

7) የኤግዚቢሽኑ ቦታ በየዕለቱ ከጠዋቱ 1 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 3:00 ሰዓት ድረስ ለተሳታፊዎች እና ጎብኚዎች ክፍት ይሆናል፤

8) የወሰዱትን ድንኳን ወይም ቦታ ለሦስተኛ ወገንሙሉ በሙሉ አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፤

9) የተሳታፊዎችን ንብረት ደህንነት ለመጠበቅ እንዲያመች ከምሽቱ 3:00 ሰዓት እስከ ከጠዋቱ 1 ሰዓት በኤግዚቢሽኑ ቦታ ከጥበቃ አባላት በቀር ማንም እንዲገኝ አይፈቀድም፡፡

## 19. የድምፅ አጠቃቀም

1) ኤግዚቢሽኑን ብሎም ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ዝግጅቶችን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ይቻል ዘንድ የበዓሉ ቦታ ለመደማመጥና መግለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት ምቹ መሆን አለበት፤

2) ተሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው እንደ ሙዚቃ፤ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፤ ፊልሞች፤ መግለጫዎች ወዘተ የመሳሰሉት ድምፅ የሚያወጡ ግብዓቶች በአካባቢያቸው ያሉትን ሌሎች ተሳታፊዎች በማያውክ ሁኔታ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፤

3) ከተሳታፊ ከተሞች የሚለቀቀው የድምጽ መጠን ከ 120 dB መብለጥ የለበትም፡፡

4) ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት እስከ ቀኑ 7:00 ሠዓት ድረስ **ለስለስ ያለ** ድምጽ ብቻ ማሰማት የሚቻል ሲሆን ከዚያ ውጪ ባለ ሰዓት የሚሰማው ድምጽ በ18.3 የተጠቀሰውን መጠን ሳያልፍና በአካባቢና በአጠገብ ያሉ ከተሞችን ሳይረብሽ የከተማውን የባህል ሙዚቃና ትርኢት ማሰማት ይቻላል፡፡

5) በ18.3 ከተገለጸው መጠን በላይ የሆኑ እና አካባቢን የሚያውኩ ድምጾችን የሚያመነጩ ተሳታፊዎች የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ የድምጽ መጠናቸውን ካላስተካከሉ የድምጽ ማጉያ መሳሪያዎቻቸውን እስከ ኤግዚቢሽኑ ፍጻሜ ድረስ እንዲያስረክቡ ይደረጋል፡፡

6) ይህን የድምጽ መመሪያ የማያከብር ከተማ ራስን በማስተዋወቅ ውድድር **መመሪያ መሰረት** እንደ አንድ መወዳደሪያ ነጥብ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

## 20. የጊዜ ሰሌዳ

1) የኤግዚቢሽን ዝግጅቱ ዋና ዋና ተግባራት በሚከተለው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይከናወናሉ፡-

| ተ.ቁ | ተግባር | ቀን |
|---|---|---|
| 1. | የአውደርዕይ ተሳትፎ ምዝገባ የቦታ መጠን ጥያቄ | መስከረም 1-መስከረም 20/ 2006 |
| 2. | የቦታ እና የምዝገባ ክፍያ | ጥቅምት 10/ 2006 |
| 3. | የኤግዚቢሽን ቦታ ዝግጅት፣ የመብራት እና ውሃ አቅርቦት፣ የአጥር ግንባታ፣ የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ፣ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ዝግጅት ወዘተ. ማጠናቀቅያ | ጥቅምት 20/ 2006 |
| 4. | የድንኳን እና ፓርቲሽን ተከላ | ህዳር 08/ 2006 |
| 5. | የኤግዚቢሽን ቦታ ርክብክብ | ህዳር 09/ 2006 |
| 6. | የኤግዚቢሽን ግንባታ ማጠናቀቂያ | ህዳር 10/ 2006 |
| 7. | የኤግዚቢሽን መክፈቻ | ሕዳር 11/ 2006 |
| 8. | የአውደርዕይ ማጠናቀቂያ | ሕዳር 18/ 2006 |

9. የአውደርዕይ ቁሳቁስ ማጓጓዝ ሕዳር 19/ 2006

# ክፍል - አምስት

## የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች እና የበጀት ምንጭ

### 21. የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች

1) የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው:ጠ

ሀ/ የቦታ ዝግጅት ወጪዎች (የቦታ ድልደላን፣ የአጥር ግንባታን፣ የመብራት እና የውሃ መስመር ዝርጋታ)

ለ/ የድንኳን እና የፓርቲሽን ኪራይ

ሐ/ የድንኳን እና ፓርቲሽን ተከላ እና ማፍረሻ

መ/ የአስፈላጊ የኤግዚቢሽን ቁሳቁሶች (ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ገመድ፣ ሁክ፣ ፕላስተር፣ ስፒል ወዘተ የመሳሰሉት ኪራይና ግዥ)

### 22. የኤግዚቢሽን ዝግጅት የበጀት ምንጭ

1) የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ኤግዚቢሽን ወጪዎች የበጀት ምንጭ ከተሳታፊ ከተሞች የተሳትፎ እና ክፍያ እና ለኤግዚቢሽኑ ዝግጅት ከአዘጋጆችና ከስፖንሰሮች የሚሰበሰበው ገንዘብ ነው::

# ክፍል - ስድስት

## ኤግዚቢሽንን ስለማስተዋወቅ እና ለተሳታፊዎች መረጃ ስለመስጠት

### 23. ኤግዚቢሽኑን ስለማስተዋወቅ

1) የከተሞች ኤግዚቢሽን በርካታ ተሳታፊዎች እና ጎብኚዎች ይኖሩት ዘንድ ጋዜጣ ሬድዮ እና ቴሌቪዥን እና ሌሎችም የማስተዋወቂያ መንገዶችን በመጠቀም ሰፋት ያለው የማስተዋወቅ ስራ በመዝናኛ ዝግጅቶችና የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ይከናወናል፤

2) ኤግዚቢሽኑን የማስተዋወቁን ስራ የሚመራው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ከመዝናኛ ዝግጅቶችና የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ነው፤

3) የኤግዚቢሽኑ የማስታወቂያ ወጪዎች የሚሸፈኑት ለኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ዝግጅት ከተመደበው በጀት ወጪ በማድረግ ነው፤

## 24. ኤግዚቢሽንን በሚመለከት መረጃ ስለማግኘት

1) ተሳታፊዎች 5ኛው የከተሞች ሳምንት በተመለከተ በስልክ ቁጥር 0115540629፣ 0115540633፣ 0115540634፣ 0115540639፣ 0115540628፣ በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡
2) ተሳታፊዎች የኤግዚቢሽን ቦታ ጥያቄ፣ የምዝገባና የክፍያን በተመለከተ ለከተሞች ጥሪ ፣መስተንግዶ እና እንግዶች ጥሪ ንዑስ ኮሚቴ ሰ.ቁ 0115-541259፣ 0115-541290 ማግኘት ይቻላል፡፡
3) **ተሳታፊዎች ለመመዝገቢያ እና ለቦታ የሚከፍሉትን ክፍያ በከተማ ልማትና ኮንስትክሽን ሚ/ር የከተማ ፕላን ጽዳትና ውበት ማስተባበሪያ ቢሮ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000000985027 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ገቢ በማድረግ በከተማው ስም ገቢ የተደረገበትን ማስረጃ በፋክስ ቁጥር 0115-54-06-30 ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት ተብሎ ኮፒው መላክ ይኖርበታል፡፡**

## 25. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከጳጉሜ 01 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 26. መመሪያውብ ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማሪያም**

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር**